# SY25-26 እና SY26-27 School Without Walls ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቅበላ ሂደት መመሪያ

ለክፍል፡ 9-12

**ማስታወሻ፥** ይህ መመርያ ለSY25-26 እና SY26-27 የተማሪ ቅበላ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**ስለ School Without Walls የቅበላ መስፈርት፥** School Without Walls ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ስኬታማ የሆነ አመልካች ሃላፊነት የሚሰማው፣ በራሱ የሚተማመን፣ ተነሳሽት ያለው፣ በየቀኑ ትምህርት ገበታው ላይ የሚገኝ፣ በትምህርቱ ላይ የሚያተኩር እና የትምህርት ፍላጎት ያለው ነው። በተጨማሪም School Without Walls ውስጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾች ራሳቸውን የቻሉ፣ ጠንካራ የሰዓት አጠቃቀም ክህሎት ያላቸው እና ዓለም አቀፍ ዜጋ የመሆን ፍላጎት ያላቸው ናቸው።

**ስለ School Without Walls የቅበላ ሂደት፥** School Without Walls ውስጥ ሁሉም አመልካቾች በቀድሞው የትምህርት ዘመን የመጨረሻ ውጤታቸው መሰረት አነስተኛውን 3.0 GPA እንዲያሟሉ እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ በሚቀርቡት ማመልካቻዎች ብዛት እና በሂደቱ የውድድር ባህሪ የተነሳ በዋናነት የኛ በጣም ብቁ የሆኑ አመልካቾች 3.5 ወይም ከዚያ በላይ ያላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፣ በመሆኑም አመልካቾች እንዲኖራቸው የሚመከረው GPA ይሄ ነው። ለዘጠነኛ ክፍል፣ ትምህርት ቤቱ የሚገመግመው GPA እና የድጋፍ ደብዳቤዎችን ነው። ከ4.0 ስኬል ከፍተኛ GPA ላላቸው ትልቅ ውጤት ላመጡ አመልካቾች የሚሰጡት የድጋፍ ደብዳቤዎች የሚገመገሙ ሲሆን ይህም ቃለ መጠይቅ ላይ እንዲሳተፍ የተጋበዘው ማን እንደሆነ ይወስናል። ለቃለ መጠይቅ የተጋበዙ አመልካቾች በቦታው ላይ በመገኘት የሚቀርብ የጽሁፍ ናሙና ላይ መሳተፍ አለባቸው። ከ 10ኛ-12ኛ ክፍል ላሉት የሚደረጉት ቃለ መጠይቆች በቀጣዩ የትምህርት ዘመን ባሉት ክፍት ወንበሮች እና በቀረቡት ማመልከቻዎች ብዛት ላይ በመመስረት ይደረጋሉ።

እያንዳንዱ የቅበላ ሂደቱ ክፍል ውጤት የሚሰጠው ሲሆን ከታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ይመዘናል። ከቅበላ ሂደቱ ክፍሎች የተገኙት ውጤቶች የያንዳንዱን አመልካች አጠቃላይ የማመልከቻ ውጤት ለማግኘት አንድ ላይ ተደምረዋል። ለቅበላ ብቁ የሚሆኑት ቃለ መጠይቁን ያደረጉ አመልካቾች ብቻ ናቸው። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| የቅበላ ክፍል | ክብደት | ማሳሰቢያዎች |
|---|---|---|
| ሪፖርት ካርድ ግምገማ (ቢያንስ 3.0 GPA ያስፈልጋል፤ 3.5 GPA ይመከራል) | የመነሻ መስፈርት | School Without Walls እንደ የሪፖርት ካርድ ግምገማ አንድ አካል ሆኖ የትምህርት ውጤቶችን ብቻ ይገመግማል። At School Without Walls ውስጥ አዲስ ገቢ አመልካቾች በኛ አታካች ፕሮግራም ውስጥ ስኬታማ ለመሆን መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ አዲስ አመልካቾች 3.0 GPA እንዲኖራቸው እንፈልጋለን፣ ነገር ግን በባለፈው ዓመት የመጨረሻ የውጤት መግለጫ ካርዳቸው ላይ 3.5 ቢኖራቸው ይበልጥ ይመከራል።<br><br>ለዘጠነኛ ክፍል፣ ከፍተኛ ውጤት ያላቸው አመልካቾች ለቃለ መጠይቅ እንዲቀርቡ ይጋበዛሉ። በDCPS የውጤት አሰጣጥ ፖሊሲ መሰረት GPA እንዴት እንደሚሰላ እዚህ ላይ ይገምግሙ።<br><br>አንዳንድ ትምህርት ቤቶች አልፏል/ወድቋል የሚል የውጤት አሰጣጥ እንደሚጠቀሙ ትምህርት ቤቱ ያውቃል። ለነዚህ አይነት አመልካቾች፣ ፍትሃዊ እና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እኩል በሆነ መንገድ የውጤት መግለጫ ካርዳቸውን ለመገምገም እንዲረዳ የውይይት መለኪያዎችን ወይም አውድ ለማግኘት የSchool Without Walls ቡድን ከትምህርት ቤቱ አማካሪዎች፣ ዲኖች፣ አመራሮች፣ ወዘተ. ጋር ግንኙነት ሊያደርግ የሚችል መሆኑን እባክዎ ልብ ይበሉ። ውይይቱ ከ40 ነጥብ በሚሞላበት ጊዜ ትምህርት ቤቱ ሁሉንም አመልካቾች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገመግም መሆኑን እና ተጨማሪ ነጥብ ለማግኘት የሚቀርቡ ልዩ ጥያቄዎች የማይስተናገዱ መሆኑን እባክዎ ልብ ይበሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| | | ሁሉም የእጣ ዙር ማመልከቻዎች ከቀረቡ እና የMy School DC ማመልከቻ ቀነ ገደብ ማብቃቱን ተከትሎ ግገማ ከተደረገባቸው በኋላ በየዓመቱ አነስተኛ የGPA መነሻ የሚወሰን መሆኑን እባክዎ ልብ ይበሉ። |
| የድጋፍ ደብዳቤ ግምገማ | 30/100 ነጥብ | School Without Walls አመልካቹ በትምህርት ቤት ላይ ያለውን ልምድ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እና ለትምህርት ውጤታቸው አውድ ለመስጠት የድጋፍ ደብዳቤዎችን ይጠቀማል። የድጋፍ ደብዳቤዎች ተማሪዎችን እና ተሞክሯቸውን በተሻለ መልኩ ለማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። School Without Walls ሁለት (2) የድጋፍ ደብዳቤዎች የሚጠይቅ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸውቢበዛ 15 ነጥብ ይይዛሉ።<br><br>አመልካቾች እባ ቤተሰቦቻቸው በነሱ ስም የድጋፍ ደብዳቤ ከሚሰጡ ግለሰቦች ጋር እንዲከታተሉ እና በተቻለ መጠን ስለአመልካቹ የተሟላ ምስል ማግኘታችንን ለማረጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤ ሰጪውን የኢሜይል አድራሻዎች ትክክለኝነት እንዲያረጋግጡ በጥብቅ እናበረታታለን። ይሁን እንጂ አመልካቾች ላልተሟሉ ወይም ለጎደሉ የድጋፍ ደብዳቤዎች የማይቀጡ ሲሆን በቀረቡ የድጋፍ ደብዳቤዎች ላይ በመመስረት ወደ ቃለ መጠይቅ ደረጃ እንዲያልፉ ሊገመገሙ ይችላሉ። |
| **ባላቸው GPA እና የድጋፍ ደብዳቤ ላይ በመመስረት፣ በያንዳንዱ ክፍል ከፍተኛ ውጤት ያመጡ አመልካቾች በቃለ መጠይቅ ላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል።** | | |
| የቤተሰብ ቃለመጠይቅ እና በቦታው በመገኘት የሚደረግ የጽሁፍ ናሙና | 60/100 ነጥብ | School Without Walls ለኛ ፕሮግራም ጥልቅ ፍላጎት፣ ለማህበረሰብ አገልግሎት ቁርጠኝነት ያላቸውን እና ትጋታቸውን በተግባር የሚያሳዩ አመልካቾችን ለይቶ በማወቅ በጥብቅ ያምናል።<br><br>ባላቸው GPA እና የድጋፍ ደብዳቤ ግምገማ መሰረት ከፍተኛ ውጤት ያመጡ አመልካቾች ለፓነል ቃለ መጠይቅ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር እንዲገኙ ይጋበዛሉ። ወይም ከአመልካች አምባሳደሮች እና/ወይም የPTO አባላት ጋር በሚደረግ ጥያቄና መልስ ላይ መሳተፍ። የቃለ መጠይቅ ፓነሉ ፋካልቲውን፣ መምህራንን እና አመልካቾችን ያካትታል። አመልካቾች እና ወላጆች ራሳቸውን በመሆን የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን!<br><br>አመልካቹን አጅቦ የሚገኘው አዋቂ ተሳትፎ ውጤት ለመስጠት በማናቸውም ሁኔታ ታሳቢ አይደረግም።<br><br>አመልካቾች የቃለ መጠይቁ አንድ አካል አድርገው በቦታው ላይ በመገኘት የሚደረግ የጽሁፍ ናሙና መሙላትም አለባቸው።<br><br>በቃለ መጠይቁ ማብቂያ እያንዳንዱ አመልካች በቦታ በመገኘት የሚቀርብ የጽሁፍ ናሙና እንዲያቀርብ ይደረጋል። በቃለ መጠይቁ መጨረሻ መመርያው እና የጽሁፍ ናሙናው ለእያንዳንዱ አመልካች ይሰጣል። ለSchool Without Walls የጽሁፍ ናሙናው ዓላማ ከጽሁፍ አገላለጽ፣ የቋንቋ እና ቃላት አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ስለሆነ የእያንዳንዱን አመልካች ክህሎት ለመመዘን ነው።<br><br>ሁሉም የአመልካች ቃለ መጠይቆች እና የጽሁፍ ናሙናዎች በአመልካቹ ውጤት ላይ 60 ነጥብ ከሚያስደምሩ ውጤቶች ጋር በተመሳሳይ ውስጣዊ ደንብ ይገመገማሉ።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ምክንያቶች፣ ቃለመጠይቆች (በምዘና ቦታው ላይ የጽሑፍ ናሙና ማጠናቀቅን ይጨምራል) ለ SY25-26 በኦንላይን ሊደረጉ ይችላሉ። |
| የ GPA እና የድጋፍ ደብዳቤ ነጥብ | 10/100 ነጥብ | ቃለ መጠይቁን ያጠናቀቁ አመልካቾች በሙሉ በሚከተለው እርከን መሰረት ባላቸው GPA ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ውጤት ይሰጣቸዋል፡<br>• 3.9 እና ከዚያ በላይ - 10 ነጥብ |

| | | |
|---|---|---|
| | | • 3.8 - 3.89 - 8 ነጥብ<br>• 3.7 - 3.79 - 6 ነጥብ<br>• 3.4 - 3.69 - 4 ነጥብ<br>• 3.0 - 3.39 - 2 ነጥብ |
| **ቃለ መጠይቅ፣ GPA እና የድጋፍ ደብዳቤ ውጤቶች ለእያንዳንዱ አመልካች አጠቃላይ የማመልከቻ ውጤት ለመስጠት አንድ ላይ ተደምረዋል። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።** | | |